# የዋሁ ተስፈኛ

በናት አገር ፍቅር ፣ የነደደው ዜጋ
በደም በአጥንጥቱ ፣ የከፈለው ዋጋ
ትግል እንዳልሆነ ፣ ቀላል፣ አልጋ ባልጋ
ጠንቅቆ ያውቀዋል ፣ ፋኖ አልተዘናጋ
ጆሮ መቼ ሰጠ ፣ ለሚል ተረጋጋ
አሁንም ጨልሟል ፣ ገና መቼ ነጋ ።

በየ ክፍለ ሃገሩ ፣ እየተዟዟረ
ሰው የሚመኘውን ፣ ስለተናገረ
ቃላት ወደተግባር ፣ ካልተመነዘረ
የወያኔን ቱባ ፣ አውርዶ ካልሻረ
ያለውን ሳይፈፅም ፣ ቀኝ ኋላ ከዞረ
መተማመን የለም ፣ ቃል በወረወረ
ሱሚ ነው ለመኖር ፣ እየተቆመረ ።

ትግላችን እንደሆን ፣ የሞትና ሽረት
አልሞ ተኳሹን ፣ ተጋፋጭ በድፍረት
እሳት የፈተነው ፣ ጠንካራ እንደብረት
ገዳዩን ለመግደል ፣ የማያሳይ ምህረት
አያውቅም ማፈግፈግ ፣ ወደኋላ መቅረት
ወሬም አይፈታውም ፣ ከንቱ ፣ ተረት ተረት ።

ይሄንን ተረድቶ ፣ አካሄዱን ይግራ
በውስጠ ታዋቂ ፣ ወያኔ እየመራ
እያስተዋልን ነው ፣ አይደለን ሸውራራ
ጠርጎ የሚወስድህን ፣ አታስነሳ አቧራ
እንዳጀማመርህ ፣ ከህቡ ጋር ስራ
ኋላ የምታዝነበት ፣ ያመጣል ኪሳራ
ወይንም ገለል በል ፣ ሁኔታው ካስፈራ ።

ምንም አልገረመን ፣ አልደነቀን እኛ
ሰይጣን ፀብ የለውም ፣ ከጂኒ መጋኛ
የትላንትም ሆነ ፣ የዛሬ ሹመኛ
አልሸሹም ፣ ዞር አሉ ፣ ባንዳና ምንደኛ
ስልቻም ቀንቀሎም ፣ አንድ ናቸው ለኛ
በቃላት ተሳክሮ ፣ ታጋዩም አልተኛ
አንገቱን ደፋ እንጂ ፣ የዋሁ ተስፈኛ ።

ታዛቢው

April 20, 2018